# ዕውነታን ያልተመረኮዘው ሰሞነኛው የአሜሪካ ሪፖርት

ዳንኤል ተዘራ 04/29/13

“ዝንጀሮ የራሷን መላጣ ሳታይ በሌላኛው ትስቃለች” ይላል የሀገራችን አርሶ አደር– አንድ ግለሰብ ወይም የህብረተሰብ ክፍል የራሱን ህፀፆች ሳይመለከት በሌላኛው ላይ ሲሳለቅ ወይም ሌላውን ለማረም ሲሞክር ሲያየው። ይህን ሀገርኛ አባባል ያነሳሁት ያለ ምክንያት አይደለም። ሰሞኑን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት (Departement of State) ኢትዮጵያን ጨምሮ የ190 ሀገሮችን የሰብዓዊ መብት አያያዝ በተመለከተ ያወጣው ኃላፊነት የጎደለው ዓመታዊ ሪፖርት እንዲሁም ቻይና በጉዳዩ ላይ “ማነው አንቺን የዓለም ዳኛ ያደረገሽ?” በማለት የሰጠችው ፈጣን የአፀፋ ምላሽ ከብዢሉ ጋር አምሳያ ሆኖብኝ እንጂ።

ታዲያ እኔም ይህን የቤጂንግን ፈጣን ምላሽ ስመለከት ‘ዕውን አሜሪካ “የዓለም ዳኛ” የመሆን ህጋዊ መብት አላትን?፣ ራሷ ከሀገሯ በማለፍ ባህር ተሻግራ እስከ ጓንታናሞ ቤይ ድረስ ስለ ምትፈፅመው የገዘፈ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ትንፍሽ ሳትል በሌሎች ላይ ለምን ጣቷን ትቀስራለች?’ የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳቴ አልቀረም። በተለይም ሪፖርቱን በደንሳሳው ሳየው በሀገራችን ላይ ያነሳቸውን የተሳሳቱና ኃላፊነት የጎደላቸውን ነጥቦች እንደ ማንኛውም ዜጋ ማረቅ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይሁንና ለሪፖርቱ ቀዳሚውን ምላሽ የሰጠችው ቻይና የጠቃቀሰቻቸውን ነጥቦች መመልከት ለአንባቢዎቼ ግንዛቤ ስለሚረዳ በቅድሚያ እሱን መመልከት ጠቃሚ ይመስለኛል። ምክንያቱም የቤጂንግ መንግሰት በራሱ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የሰጠው ምላሽ “ዓይንህ ውስጥ ያለውን ትልቅ ግንድ ሳታይ፣ በሌሎች ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አትሞክር” የሚል መልዕክት ያለው ከመሆኑም በላይ፤ ቀደም ሲል ያነሳኋቸውን ጥያቄዎች ከበቂ በላይ ስለሚመልስልኝ ነው።

የቻይና መንግስት ‘ዥንዋ’ በተሰኘው የሀገሩ የዜና አውታር አማካኝነት እንደገለፀው፤ አሜሪካ የራሷን ዜጎች ትሰልላለች፣ በሴቶችና በአናሳ ብሔሮች ላይ ጭቆና ታካሂዳለች እንዲሁም በመሳሪያ አማካኝነት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆኑ ፈቅዳለች። እናም የዋሽንግተን አስተዳደር “የዓለም ዳኛ” የመሆን ምንም ዓይነት መብት የሌለው በመሆኑ ራሱ የሚፈፅውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ችግር በተሻለ መንገድ መፍታት ይኖርበታል ብሏል። አክሎም ሪፖርቱ የአሜሪካ መንግስት ራሱ የሚፈፅመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳላየ

በማለፍ አንዲትም ቃል ትንፍሽ አላለም ሲል ተችቶታል። አሜሪካ ውስጥ የሃይማኖት ልዩነት መኖሩን የሚያትተው የቤጂንግ ምላሽ፤ በተለይም በሙስሊሞች ላይ የሚፈፀመው ጥቃትና ዘለፋ በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ መምጣቱንም አትቷል። የኦባማ አስተዳደር የሀገራትን ደህንነት በመፃረር የስለላ ስራም ያከናውናል።

እንግዲህ ይህ በጥቂቱ የተመለከትነው የቻይና መንግስት ምላሽ በዋነኛነት የሚያጠነጥነው፤ የዋሽንግተን አስተዳደር ስለማንኛውም ሀገር ላይ መግለጫ ወይም ሪፖርት የማውጣት ህጋዊ መብት የሌለው መሆኑን፣ ራሱን ከደሙ ንፁህ አድርጎና በሀገሩ የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ሳይናገር በፍርደ-ገምድልነት በሌሎች ላይ ጣቱን መቀሰሩን እንዲሁም ሪፖርቱ ራሱ ሚዛናዊ ያልሆነና ለራስ ያደላ፣ የሀገራትን መብት የሚጋፋ ብሎም የአንድን ሀገር ሉዓላዊት በመጣስ የስለላ ስራ በማከናወን ጭምር የተገኘ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው።

በእኔ እምነት ግን ሪፖርቱ ከዚህ በዘለለም ተጨባጭነት በሌላቸውና በሐሰት ላይ በተመሮዙ የተሳሳቱ መረጃዎች የታጨቀ ጭምርም ነው። በተለይም ሀገራችንን አስመልክቶ የተጠቀሱት ጉዳዩች ከነባራዊው ዕውነታ እጅግ ያፈነገጡ ናቸው። እናም ለእነዚህ የተሳሳቱና በአስገራሚ ሁኔታ የራሱን ኒዮ-ሊበራላዊ አጀንዳ ይዞ የሚንቀሳቀሰውን ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለን ከስሙ ጋር የማይተዋወቅ ውሽታም ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጅትን በማጣቀሻነት በመጠቀም በሪፖርቱ ውስጥ የተሰገሰጉ አባባሎችን እንደ ዜጋ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። በመሆኑም ሌላው ቢቀር ለአንድ ሪፖርት የማያወላዱ ግብዓት ናቸው ከሚባሉት ነጥቦች ውስጥ አንዱ የሆነውን የመረጃ ምንጭ ትክክለኛነትን በማየት ብቻ የሪፖርቱን ጥቅል ይዘት ልንመለከት እንችላለን።

እንደሚታወቀው ሂዩማን ራይትስ ዎች የተሰኘውና 'ኒዮ-ሊበራሊዝምን የግድ ካልተቀበላችሁ በየጊዜው የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሂድባችኋለሁ' የሚለው የርዕዮተ-ዓለም አክራሪ ቡድን ፤ በየጊዜው ከፖለቲካ ፍላጎቱ በመነሳት በሀገራችን ላይ እንደ ሐምሌ ዝናብ ሳያቋርጥ የሚያዘንባቸውን የሪፖርት ጋጋታዎች ራሷ አሜሪካ ያለችበት የለጋሽ ሀገራት ቡድን (DAG) በመስክ ቅኝቱ ውሸት መሆኑን አረጋግጧል። እናም የዋሽንግተን አስተዳደር የዚህን የቅጥፈት አለቃ ተራ ልቦለድ እንደምን የሪፖርቷ ማጣቀሻ እንዳደረገው ከሪፖርቱ አዘጋጅ ውጪ ለማንም ግልፅ የሚሆን አይመስለኝም። በመሆኑም እዚህ ግባ የሚባል ተቀባይነት ሊኖረውም አይችልም–የመረጃ ምንጩ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ ተቋም ነውና።

ከዚህ በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ሪፖርት ሀገራችን ውስጥ ራሱ የመደበውን የ"ዳግ" አባልንና ትክክለኛ የመስክ ቅኝቱን በመፃረር ከራሱ ድብቅ አጀንዳ በመነሳት ምንም ዓይነት ጥናት ሳያካሂድ ያለምንም ማስረጃ አሉባልታን የሚያራግብ ቡድንን በእማኝነት የተጠቀመ

በመሆኑ ከፈጠራ ድርሳንነት ተለይቶ የሚታይ አይደለም። እናም እንዲህ ዓይነቱ ሪፖርት ቻይና እንዳለችው በየትኛውም ህጋዊ ማዕቀፍ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ያወጣው ሪፖርት ካለፉት ዓመታት ብዙም የተለየ አይደለም። የተለመደና አሰልቺ ነው—"ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ አለ" እንዲሉት ዓይነት። ትናንትን በዛሬ፣ ዛሬን በትናንት መነፅር የሚያይ እዛው ረጋጭ መግለጫ። ግና ምናልባት የሪፖርቱ ባለቤቶች የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን የቅጥፈት ሪፖርቶች በየዓመቱ በማስተጋባት "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" የሚለውን አሮጌን የፕሮፖጋንዳ ዘዴ ለመጠቀም አስበው ከሆነ፤ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ማን ምን እንደሆነ ፍንትው ብሎ በሚታወቅበት በዛሬው ዘመነ ግሎባይላይዜሽን ወቅት እንዲህ ዓይነቱ ተቀባይነት የሌለው አካሄድ የሪፖርቱን ትክክለኛነት ገደል ከመክተት በዘለለ ውሃ ሊቋጥርላቸው የሚችል አይመስለኝም። ለምን ቢባል፤ በሪፖርቱ ውስጥ በመረጃ ምንጭነት የተጠቀሱት ቡድኖች ትክክለኛነታቸው አጠራጣሪ እንዲሁም ገለልተኝነት የሌላቸው በመሆኑ ነው። እናም ሪፖርቱ አሉባልታን እንጂ ዕውነታን ተመርኩዞ የተዘጋጀ ነው ሊባል አይችልም።

ያም ሆነ ይህ ግን እኔም ቀደም ባሉት ዓመታት በወጡት ሪፖርቶች ላይ የነበሩትን በወተውና ራሴን በአዳዲሶቹ ፈጠራዎች ላይ በመወሰን ሪፖርቱን ተመልክቼዋለሁ። በመሆኑም ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ሱስ ከተጠናወተውና አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋም ከሆነው የሂዩማን ራይትስ ዎችን የተለመደ ማላዘን ተመርኩዞ ወይም ከሀገራችን ተላላኪ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች የተቃረሙ አሊያም የቤጂንግ መንግስት እንዳለው 'በስለላ' መልክ የሰብዓዊ መብት ሪፖርት ማዳበሪያ ለመሆን የበቁትን በሐሰት የጎለሙሱ ባለ 41 ገፅ የቃላት ድሪቶዎችን በጥቂቱም ቢሆን እየነቀስኩ ሃቁን እንዲህ ላስቃኛችሁ እሞክራለሁ።…

በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ የተዘጋጀው ሪፖርት በዋነኛነት በኢትዮጵያ ሀሳብን በነጻነት የመግለፅና የመሰብሰብ መብት መገደቡን ያትታል። መንግስት ፖለቲካዊ ይዘት ያለውን ክስ በመመስረት በተቃዋሚዎች፣ በጋዜጠኞች፣ በአክቲቪስቶችና በጦማሪዎች ላይ ጫና እየፈጠረ እንደሚገኝ እንዲሁም በህትመት ሚዲያው ላይ ገደቦች መጣላቸውን ይገልፃል። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮ- ቻናል እና ፍትህ…ወዘተ. ጋዜጦች መዘጋታቸውን ገልጿል። …ውድ አንባቢዎቼ! እስቲ የእነዚህን አባባሎች ትክክለኛነት እንመልከት።…

በመጀመሪያ ደረጃ በሀገራችን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅና የመሰብሰብ መብቶች በህገ-መንግስቱ ዋስትና ያለው ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ በመሆን ላይ ያሉ የማይሸራረፉ ጉዳዩች እንደሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ዜጋ የመሰለውን ሃሳብ የማራመድና በፈለገው ዓይነት ድርጅቶች ውስጥ ታቅፎ የመደራጀት ብሎም የመሰብሰብ ህጋዊና ተግባራዊ መብት አለው። አንድ ሰው ሃሳቡን በመግለፁ አሊያም ለምን እዚህ ድርጅት ውስጥ

ገብተህ ተሰበሰብክ? ተብሎ የሚጠየቅበት አግባብ ሀገራችን ውስጥ የለም። ይህን ደግሞ ሁሉም ዜጋ ተግባራዊ እያደረገው ለመሆኑ ሀገር ቤት ብቅ ብሎ ሃቁን ከትክክለኛው መረጃ በማየት ማረጋገጥ የሚቻል ይመስለኛል።

እርግጥ ማንኛውም መብት ህጋዊ ማዕቀፍ የሚበጅለት መሆኑን ባለ ሪፖርቶቹ የሚዘነጉት አይመስለኝም–እነርሱም ራሳቸው ተግባራዊ ያደርጉታልና። ስለሆነም የሀገርን ደህንነትና ፀጥታ በሚፃረር መልኩ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ከመናገርና ከመሰብሰብ ባለፈ ችግር ቢፈጥር መብቱ ስላለው ብቻ ምንም ዓይነት ህግ ሊዳኘው አይችልም ተብሎ ዝም አይባልም። ለአብነት ያህል በአስከፊነቱ ሁላችንም ባወገዝነው በሰሞነኛው የቦስተኑ የሽብር ጥቃት፣ ሁለቱ ወንድማማቾች በአንድነት ተሰብስበው በአሜሪካ ደህንነት ላይ ጥቃት በመፈፀማቸው ተገቢውን ህጋዊ ቅጣት ማግኘታቸው አግባብነቱን የምንመለከተው የሀገርንና የህዝብን ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ መሆኑ ሊዘነጋ የሚገባው አይመስለኝም። እናም እኔ እስከማውቀው ድረስ በሀገራችን ውስጥም እንዲህ ዓይነቱ ፀረ-ሀገርና ህዝብ ተግባር በተገቢው የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ታይቶ ተግባራዊ ካልሆነ በስተቀር፤ ማንኛውም ዜጋ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሃሳቡን ይገልፃል፤ ይደራጃል፤ ይሰበሰባል። ከዚህ ውጪ የሪፖርቱ ተቃራኒውን ሃሳብ ከወዴት እንዳመጣው ለራሱም ግልፅ የሚሆን አይመስለኝም።

እዚህ ላይ ግን አንድ ሳልጠቅሰው የማላልፈው ዕውነታ አለ። ይኸውም የሀገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ባህል ግንባታ ገና ለጋና ታዳጊ በመሆኑ እንዲሁም ፈፃሚዎቹ ሰዎች በመሆናቸው ብሎም ልክ እንደ አሜሪካ ከ200 ዓመታት በላይ ባለማስቆጠሩ ተግባራቱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም። ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ለነገሩ እንኳንስ እኛ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ ገና 21 ዓመታትን ያስቆጠርን ሀገር ቀርቶ፤ ከሁለት ክፍለ ዘመናት በላይ ያስቆጠረችው የሪፖርቱ ባለቤትም ብትሆን በርካታ የዴሞክራሲ ተግዳሮቶች ውስጥ የታጠረች ናት– ቀደም ሲል እንደ ጠቀስኩት ሰሞነኛው የቻይና ምላሽ ከሆነ። ይሁንና ሀገራችን ዴሞክራሲን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመገንባት ረጅም ጊዜ ይወስዳል ብላ እጇን አጣጥፋ አልተቀመጠችም። እናም ከዴሞክራሲ ጀማሪነቷ አኳያ ሊኖሩ የሚችሉ ህፀፆችን በሂደት እየቀረፈች መጥታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከትላንት ዛሬ የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሰች እንጂ፤ መሰረታዊ የሰው ልጅ መብቶች የሚገደቡባት ሀገር እንዳልሆነች በቅንነት መገንዘብ ተገቢ ይመስለኛል።

መንግስት በማናቸውም በሀገሪቱ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ /በተቃዋሚዎች፣ በጋዜጠኞች፣በአክቲቪስቶችና በጦማሪዎች/ ላይ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ክስ ይመሰርታል የሚለው የሪፖርቱ ስሞታም መሰረተ-ቢስና ህግን ያላማከለ ነው። አንድ ዜጋ ወይም ቡድን ተቃዋሚም ይሁን አራሚ፣ አራሽም ይሁን ቀዳሽ አሊያም ተኳሽ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ህጎች ተላልፎ እስካልተገኘ ድረስ መጠየቁ የግድ ነው። የህግ የበላይነት መረጋገጥ አለበትና። ለአብነት ያህል በሪፖርቱ ላይ የተጠቀሱትን የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የሆኑትን አቶ አንዷለም

አራጌንና ጋዜጠኛም ሆነ ጦማሪ ያልሆኑትን አቶ እስክንድር ነጋን ብንወስድ እንኳን፤ እነዚህ ወገኖች የታሰሩት የሀገሪቱን ህጎች ተላልፈው ሽብር ለመፈፀም በማሴራቸው እንጂ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል አሊያም ሪፖርቱ እንዳለው በጋዜጣ ላይ በፃፉት ሪፖርት ምክንያት አይደለም። በሀገሪቱ ህግ መሰረት ግለሰቦቹ ያከናወኑት ተግባር በሽብርተኝነት ያስጠየቃቸው በመሆኑ ሊታሰሩ ችለዋል። በዚህ ፀሐፊ እምነት በፀረ-ሽብር እንቅስቃሴ ከሀገራችንም ይሁን ከሌሎች ሰላም ወዳድ ሀገራት ጋር በጥብቅ የምትሰራው አሜሪካ ለአሸባሪዎች ወግና ‘እነ እገሌ ለምን ታሰሩ?’ የሚል በአቋም ደረጃ ማንፀባረቋ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ኢ-ፍትሃዊ ተግባርም ጭምር ነው።

ማንም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበውና በአንድ ወቅት ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ ለፓርላማ እንደተናገሩት፤ የነጮች ደም ቀይ ነው፣ የጥቁሮችም ደም ቀይ ነው። አንድ ግለሰብ አሸባሪነቱ ለአሜሪካ ካልተገለፀላት የሌላን ሀገር ሉዓላዊነት እየጣሰች እንደ ንፁህ የምትቆጥርበት አግባብ ሊኖር አይችልም። አሸባሪ ያው አሸባሪ ነውና።...ኸረ ለመሆኑ የዋሽንግተን መንግስት በራሱ ህግ በአሸባሪነት የፈረጃቸውን እንደ አል-ቃዒዳ ዓይነት አሸባሪዎችን ሌሎች ሀገራት ‘የለም ቡድኑ ንፁህ ነው!’ የሚል አቋም ቢይዙ ከቶ ምን ይል ይሆን?–አዎ! ሀሳቡን እንኳንስ ሊቀበለው ቀርቶ ሊሰማውም የሚፈልግ አይመስለኝም። ኸረ እንዲያውም በሀገራቱ ላይ ሌላ እርምጃ ሊወስድ አለመቻሉን ማንም እርግጠኛ ሊሆን አይችልም። እናም የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ሪፖርት “በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት ከመሆን የሚዘል አይደለም። ስለሆነም ”አንድ አሸባሪም ሆነ ህግ ለአሜሪካ ሲሆን ተቀባይነት ያለውና በትክክል የሚሰራ፤ ለሌላው ከሆነ ደግሞ እንደ ችግር ተቆጥሮ “የስም ማጥቆሪያ” ሪፖርት የሚወጣበት ሊሆን አይገባም ባይ ነኝ።

በሪፖርቱ ላይ ከሰፈሩት ጋዜጦች መካከል ኢትዮ-ቻናልም ይሁን ፍትህ ጋዜጣ የተዘጉበትን ምክንያት በመንግስት ላይ ለመለጠፍ መሞከርም ተገቢነት ያለው አይመስለኝም። እኔ እስከማውቀው ድረስ ኢትዮ-ቻናል ጋዜጣ የተዘጋው ከግብር ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው። መቼም ለአሜሪካ መንግስት ስለ ግብር ወይም ስለ ታክስ ማውራት ለቀባሪው የማርዳት ያህል ሆኖ ነው የሚሰማኝ–በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው አቋም ጠንካራ ነውና። እናም አንድ ድርጅት ለመንግስት ግብር አይክፈል የሚል አይመስለኝም። ግና ጋዜጣው እንዴት ሊዘጋ እንደቻለ በቅጡ ሳያጣራ እንኳን ጉዳዩን ለኢትዮጵያ መንግስት ጥሩ ዕይታ ከሌላቸው አካላት እንደወረደ ተቀብሎ ለሪፖርት ፍጆታነት ማዋሉ ትዝብት ላይ የሚጥለው ይመስለኛል። ምክንያቱም አሜሪካ ውስጥ ግብር የማይከፍል ማንኛውም ተቋም ከመዘጋት አልፎም ሌላ ጣጣ የሚከተለውም ጭምር በመሆኑ ነው። እኛ ሀገር የሆነው ግን ጋዜጣው ያለበትን የግብር ዕዳ ከፍሎ ወደ ስራው እንዲመለስ ነው የተደረገው። ያም ሆኖ ግን የጋዜጣው ችግር ተፈትቶ (ያለበትን የመንግስት ግብር ከፍሎ ሊሆን ይችላል) ወደ መደበኛ ስራው ተመልሷል–ምንም እንኳን ሪፖርቱ ይህን ለመግለፅ ዳተኛ ቢሆንም።

ፍትሕ ጋዜጣም ቢሆን ልክ በሌሎች ሀገራት ሚዲያዎች ከማተሚያ ቤቶች ጋር በሚያደርጉት ውል መሰረት፣ ያሳትምበት ከነበረው ማተሚያ ቤት ጋር በተፈጠረ አለመግባባት የተቋረጠ ነው። መንግሰት ደግሞ አንድን በነፃነት የሚንቀሳቀስ ተቋም አሰራር ውስጥ ገብቶ 'ይህን አድርግ አሊያም ይህን ፍጠር' ሊል የሚችልበት አሰራር የለም–የማንኛውም ድርጅት የአሰራር ነፃነት መከበር ይኖርበታልና። በሌሎች ሀገሮች ውስጥ የሚፈፀመውም ይኸው ነው። እኛ ሀገር ውስጥ አሰራሩ እንደ ተዓምር ተቆጥሮ ለሪፖርት ማዳበሪያ እንዴት ሊውል እንደቻለ የሚያውቁት የሪፖርቱ ባለቤቶች ብቻ ናቸው።

ታዲያ በእነዚህ ክንዋኔዎች የኢትዮጵያ መንግስት ሊመሰገን እንጂ የሪፖርት ሰለባ ሊሆን የሚገባው አይመስለኝም። እርግጥም መንግስት ሆደ ሰፊና ቻይ ነው ማለት ይቻላል። እርግጥም አሜሪካ ውስጥ የአል-ቃዒዳ የሽብር ጥሪ አሊያም አስተዳደሩ መሰማት የለባቸውም የሚላቸው አጀንዳዎች እንደማይተላለፉት ሁሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥም መንግስት በትግዕስት የሚያልፋቸው የአሸባሪዎችን አጀንዳ የሚያራምዱ ወይም ለሀገሪቱ ደህንነት አደጋ የሆኑ መልዕክቶች እንዳይተላለፉ ቢታገዱ አዲሱ ነገር ምንድነው?...አንድን የሚዲያ ውጤት አሜሪካ ከብሔራዊ ጥቅሟ አንፃር ስታግደው አግባብነት ያለው፣ ተግባሩ በሌላ ሀገር ውስጥ ሲፈፀም ደግሞ ተገቢ የማይሆንበት ህግ ከወዴት የመጣ ይሆን?...መቼም ያስተዛዝባል ከማለት ውጪ ሌላ ማለት የሚቻል አይመስለኝም።

ሪፖርቱ በዚህ ብቻ አላበቃም። በሐምሌ ወር ላይ "መንግስት በሀይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል" በሚል ሰልፍ በወጡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ፖሊሶች አላስፈላጊና ሀይል የተቀላቀለበት እርምጃ ወስደዋል፣ በርካቶችን ለእስር ዳርገዋል ሲልም ገልጿል።...

ሃቁ ግን ይህ አይደለም። እንደሚታወቀው በኢፌዴሪ ህገ -መንግስት አንቀፅ 11(3) ላይ "መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም" የሚል ጉልህ ድንጋጌ ሰፍሯል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሁለት መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳቦችን የያዘ ነው፡፡ አንደኛው፣ መንግስት በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ ገብቶ "ይህኛው ትክክል ነው፣ ያኛው ደግሞ የተሳሳተ ነው" የሚል ብያኔ የመስጠት መብት የሌለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ማንኛውም ሃይማኖት በመንግስት አሰራሮች ውስጥ በመግባት "ይህን አድርግ፣ ያንን አታድርግ" በማለት ጣልቃ ገባዊ ተግባርን እንደማያከናውን የሚያመላክት ነው፡፡ እስካሁን ድረሰም የሀገራችን መንግስት በጥብቅ ሲመራበት የመጣው እሳቤም ይኸው መሆኑ አይታበይም።

የሪፖርቱ መሰረታዊ ስህተት የሚመነጨው ግን ምናልባትም መንግስት የተባለውን ነገር የፈፀመው "በሃይማኖታችን ጣልቃ ገብተሃል?" ባሉ ግለሰቦች ላይ ነው ወይስ "ሃይማኖትን በግርዶሽነት ተከልለው የሀገሪቱን ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲን ለማደናቀፍ እኩይ ሴራን አንግበው በተንቀሳቀሱ ጥቂት አክራሪዎች ላይ ነው?" የሚሉትን ዕውነታዎች አለመመርመሩ ነው። እንደ

እውነቱ ከሆነ መንግስትን ያለ ባህሪውና ያለ ተፈጥሮው እየመዘኑ 'በሃይማኖቴ ውስጥ ጣልቃ ገብተሃል' ያሉ ወይም የሚሉ ግለሰቦችን እኔ በበኩሌ አላስታውሳቸውም፤ ይኖራሉ ብዬም አላስብም። ይልቁንሰ እዚህ ሀገር ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሃቅ የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ 'የኢፌዴሪ መንግስት ባለፉት ስርዓቶች የተነጠቅነውን የእምነት ነፃነትና የሃይማኖት እኩልነትን አሰፈነልን፣ በርካታ መሳጊዶችንና ቤተ-አምልኮዎችን እንድንገነባ አደረገን…ወዘተ.' ሲል ማድመጥ የተለመደ መሆኑ ነው። እናም ነባራዊውን ሃቅ ወደ መሬት ወረድ ብሎ ማየት የሚጠይቅ ይመስለኛል።

ሆኖም የሪፖርቱ ፍላጎት መንግስት ይህን የእምነት ነፃነት ተፃርረው ሃይማኖትን እንደ ምሽግ በመቁጠር ሀገራዊ አደጋን ደቅነው በነበሩ ጥቂት ከሽብር ጋር ቁርኝት በነበራቸው ግለሰቦች ላይ ለምን እርምጃ ወሰደ? የሚል ከሆነ ክርክሩ ጉንጭ አልፋ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ሌላው ቢቀር ነገርዬው "በራስህ ላይ እንዲፈፀም የማትፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አትፈፅም" የሚለውን ሞራላዊ እሴት (Moral value) የሚፃረር በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። ጉዳዩን ከነባራዊ ዕውነታ አኳያም ስንመለከተውም፤ በአል-ቃዒዳው መሪ ኦሳማ ቢን ላደን ላይ የተወሰደው እርምጃ አሊያም ወንድማማቾቹና አፍጋኒስታን ሄደው ስልጠና መውሰዳቸውን የሰማንላቸው ሁለቱ የቦስተን አሸባሪዎች ላይ የተፈፀመው ድርጊት አግባብነት የሌለው ነው የሚል እንድምታን እንድንይዘ ያደርጋል። ይህ ደግሞ በማንኛውም ስሌት ትክክል አይደለም። በመሆኑም ኢትዮጵያን እስልምናን የተጠለሉ ጥቂት አሻባሪዎች እስላማዊ መንግስት ለመመስረት እንደ ናይጄሪያው ቦኮ ሃራም እንዲሁም እንደ ማሊው አንሳር ዲን እንዳሻቸው ሲፈነጩ የሃይማኖት ነፃነት ስለሆነ ምንም ዓይነት እርምጃ አትውሰጂ የሚል ሪፖርት- ቀመስ ህግ ሊኖር አይችልም።

እኔ የምለው ግን በሰለጠነችውና የነፃነት ተምሳሌት መሆኗ በሚነገርላት አሜሪካ ውስጥ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩትና ቻይና እንዳለችው የሃይማኖት ልዩነት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ፣ በተለይም ሙስሊሞች በሚንገላቱበትንና ጥቃት የሚፈፀምባቸውን ሁኔታ በጉያዋ ውስጥ ይዛ ለምን በሌሎች ጥቃቅን ጉዳዩች ውስጥ ትገባለች?– እዚህስ ላይ አሜሪካ እኔ ፍፁምና ኤልሻዳይ ነኝ፣ የማደርገውም ነገር ሁሌም ስህተት የለውም እያለችን ይሆን እንዴ?…መቼም ወቸው ጉድ እንጂ ሌላ ምን ይባላል?!…

ራሱን በማሸሽና ተጨባጭ ሃቆችን በመሸሽ ላይ የተመሰረተው ሪፖርቱ ሌላው ያነሳው ጉዳይ ቢኖር፤ የሀገራችንን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅን በመተቸት ያቀረበውና 'እኛን ምሰሉ' አባባል ነው–የኢትዮጵያ መንግስት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የሲቪል ማህበራትን ለመቆጣጠር ያወጣው ህግ አሁንም መቀጠሉንና ገደቡም ፀንቷል በማለት።… ይህ አግባብ ያልሆነ ትችት በመጀመሪያ ደረጃ በአንዲት ሉዓላዊት ሀገር ውስጥ ጣልቃ በመግባት

ህጋችሁን ቀይሩ የሚል በመሆኑ ከሀገራት በመከባበር ላይ የተመሰረተ የግንኙነት መርህ አኳያ ቅቡል አይመስለኝም። በሌላ መልኩም የትኛውም ሀገር ቢሆን ሌላውን ሊመስል አይችልም። አንዱ የሚከተለው ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና ከሌላው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብሮ ሊሄድ አይችልም። ከዚህ አንፃር አሜሪካ የልማታዊ ዴሞክራሲን ፍልስፍና ካባን ልበሺ ብትባል ስለሚጠባት እምቢኝ እንደምትል ሁሉ፤ ሀገራችንም የማይበቃትን የኒዮ-ሊበራሊዝምን ጥብቆ ተሰፍቶልሻልና የግድ መልበስ አለብሽ ልትባል አይገባትም—አይሆናትምና። እናም አዋጁ ከዚህ ሃቅ አኳያ መታየት ይኖርበታል ባይ ነኝ።

እንደሚታወቀው የዚህ አዋጅ ጉዳይ "የሁለት ዓለም" ፖለቲካዊና ርዕዩተ-ዓለማዊ ትግል በመሆኑ፤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና ከወጣበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ የሀገራችን መንግስት በገዛ ሀገሩ ውስጥ ህግን የመደንገግ ኃላፊነት እንደሌለው በመቁጠር፤ ሲያሻቸው "በሰብዓዊ መብት ሽፋን"፣ በል ሲላቸው ደግሞ "በዴሞክራሲ ቀኖና" አሊያም "የብዙሃን ማህበራት ታፈኑ" በሚሉ መሰረት የሌለው ስሞታና ውዥንብር በመፈጥሩ ሃይሎች ሲናጥ ከርሟል። ከፋቱ ይህ አጀንዳ የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች መሆኑ የታወቀ፤ የአሜሪካ መንግስት አውቆም ይሁን ሳያውቅ እንደ ትክክለኛ መረጃ ቆጥሮት በሪፖርቱ ውስጥ ማካተቱ ነው።

ግና የአዋጁ መውጣት ለሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ዕድገቶች ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ መንግስት ያወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል የተዘጋጀ በመሆኑ፤ የሀገራችን ፖለቲካ ከኪራይ ሰብሳቢነትና ከፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ነፃ እንዲሆን የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አዋጁ በሀገራችን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሀገር በቀልና የውጭ በጎ አድራጊ ድርጅቶች በሀገሪቱ የልማት ስራዎች ላይ በስፋት እንዲሳተፉ፣ ዜጎች ባቋቋሟቸው ማህበራት ተደራጅተው በንቃት የሚንቀሳቀሱበትን ማዕቀፍ የፈጠረና ወደፊትም እንዲፈጥር ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

ሆኖም "ለትርፍ ያልተቋቋመ" የሚል ስያሜ የተቸራቸው የውጭ "መያዶች" እንዲሁም በገንዘብ ኃይል እንደአሸን የሚፈለፍሏቸው የሀገር ውስጥ "በጎ አድራጊዎችና ሲቪክ ማህበራት"፤ በሀገራችን የውስጥ ፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ ብሎም "እውነተኛ በጎ አድራጊዎች" ሆነው በነጻነት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ለማድረግ የወጣውን አዋጅ በጽኑ ሲኮንኑ የነበሩ መሆናቸውን የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ግና የተቃውሟቸው ዓላማ ድብቅ አጀንዳቸውን ራቁቱን ስለሚያስቀር እንጂ አዋጁ ትክክል ስላልሆነ እንዳልነበር ማስረጃን አስደግፎ መመልከት ይቻላል።

የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያስታውሰው ከዛሬ ዓመት በፊት በሀገረ ግብፅ የነበሩት የውጭ "መያዶች" ሲያከናውኑት በነበሩት ህገ-ወጥ ተግባር ምክንያት ክስ እንዲመሰረትባቸውና አባሎቻቸው ከግብጽ ልሳነ-ምድር እንዲወጡ እንዲሁም በወንጀል እንዲከሰሱ ተደርገዋል። ተቋማቱ ከሂዩማን

ራይትስ ዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ሲሆን፤ መጠሪያቸውም “ዓለም አቀፍ የሪፐብሊካን ተቋም (IRI)”፣ “የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ተቋም” (NDP) እና “ ፍሪደም ሃውስ” የተሰኙ የአሜሪካ ድርጅቶች ናቸው፡፡

እርግጥ በእነዚህ ተቋማት ተቋማት አማካኝነት በግብፅ የታየው ህገ-ወጥ ተግባር “መያዶች” ከመጋረጃው በስተጀርባ ሆነው የሚተውኑትን ድራማ ብቻ አይደለም ያሳየን። እስከ ዛሬ ድረስ ሀገራችንን በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጆች ዙሪያ የሚያብጠለጥሉበት እውነተኛ ምክንያታቸው ምን እንደሆነም ጭምር የሚያመለክት ነው፡፡ “ስለ ዴሞክራሲ እንሰብካልን” የሚሉት እነዚህ ኃይሎች ሰውነታቸውን ሰደው የአንድን ሃገር ሉዓላዊነት በመጻረር፤አለመረጋጋትን በመፍጠር አለያም ያልተረጋጋ ህብረተሰብ እንዲኖር በማድረግ የራሳቸውን የኪራይ መሰብሰቢያ ኮሮጆዎችን ለመሙላት በመንግስት ግልበጣ ጭምር የሚሳተፉ እንደሆኑም ግልፅ ነው፡፡ እናም በእኔ እምነት ቀደም ሲል እንደጠቀስኩትና የቻይና መንግስት እንዳለው ምናልባትም የዋሽንግተን አስተዳደር የሀገራትን ደህንነት በመፃረር የስለላ ተግባራትን ላለማከናወኑ ማንም ማረጋገጫ የሚሰጥ አይመስለኝም።

ያም ሆነ ይህ ግን የዓለም አቀፍ የሪፐብሊካን ተቋም ዳይሬክተርና የአሜሪካ የትራንስፖርት ሚኒስትር ልጅ የሆኑት ሚስተር ሳም ላሁድን ጨምሮ ስምንት አሜሪካውያን፣ ሦስት ሰርባውያን፣ ሁለት ጀርመናውያን፣ አንድ ኖርዌጅያዊና አንድ ፍልስጤማዊ በአስቸኳይ ካይሮን ለቀው እንዲወጡ የተደረጉበት የግብፅ እርምጃ፤ የመያዶቹንና የአባሎቻቸውን ማንነት ያረጋገጠ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገርም የኢትዮጵያ መንግስት ያጸደቀው “ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ” ትክክለኛ መሆኑን በማያሻማ ቋንቋ የተናገረ ጭምርም ይመስለኛል፡፡ እናም ከእነዚህ ሀገራዊ ጠቀሜታዎች አኳያ በሪፖርቱ አዋጁን ለመተቸት የሞከረበት መንገድ ትክክል ያልሆነ ብቻ ሳይሆን ለራስ ፍላጎት ቅድሚያ የሰጠ ነው ቢባል ሃቁን መሳት አይሆንም። “ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ” እንዲል የሀገራችን ሰው።

አሜሪካን ከሚያክል ትልቅ ሀገር የወጣው ይህ ሪፖርት፤ የአገም-ጠቀም ሰለባ ሆኖ እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ጉዳዮችንም በውስጡ አካትቷል። የጉዳዩቹ አንኳር ነጥብ ደግሞ ከሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ላይ እንደወረደ የተገለበጠው ያው የፈረደበት የጋምቤላው የዜጎች ሰፈራ ነው። ሪፖርቱ በአንድ በኩል የሰፈራው ፕሮግራም የተካሄደው በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ቢሆንም በፕሮግራሙ ላይ ግን በመንግስት ቃል የተገቡት የመሰረተ-ልማት አውታሮች ያልተሟሉ መሆናቸውን ከለጋሽ ሀገራት መረዳቱን እየገለፀ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ሂዩማን ራይትስ ዎች ሰፈራው ያለ ፈቃደኝነት ነው የተካሄደው ብሏል ይላል። ነገሩ የተምታታ ነው። የሪፖርቱ ባለቤት

ሚዛናዊ ዕይታ እንኳን የለበትም። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን የአሜሪካ መንግስት ለራሱ የሚሰሩለትን የሊጋሽ ሀገራት ተወካዩቹን በዚህም ክንዋኔ ለማመን መቸገሩን ነው።

በዚህም አለ በዚያም ግን ስለ ሰፈራው ያለው ትክክለኛ መረጃ ወዲህ ነው—ከእኛ ወዲያ ስለ ልማታችን የሚናገርና በትክክል የሚገልፅ ሊኖር አይችልምና።... ሁላችንም እንደምረዳውና ሪፖርቱም ለጋሽ ሀገራትን ጠቅሶ እንዳልካደው በጋምቤላም ይሁን በሌሎች ክልሎች የተካሄዱትና ወደፊትም የሚካሄዱት የሠፈራ ፕሮግራሞች በግዳጅ ላይ የተመሰረቱ አልነበሩም፤ አይደሉምም፡፡ ይህን ሃቅ ከባህር ማዶዎቹ አራጋቢዎች በተሻለ የምናወቀው እኛ ኢትዮጵያዊያን ነን፡፡ ሰፈራው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንዲሁም  የራሱ  ህግና ስርዓት ያለው መሆኑን በቅርበት የምናስተውለው ዕውነታ ነው፡፡ እናም ሃቁን እንነጋገር ከተባለ ዜጎች ወደ ሰፈራ ጣቢያ የሚሄዱት በራሳቸው ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው የራሳቸውንም ይሁን የሀገራቸውን ትልም ዕውን ለማድረግ እንደሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚመሰክረው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም መንግስት ዜጎችን ለም ወደሆኑ አካባቢዎች የሚያሰፍረው ሀገራችን የተያየዘችውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ገቢራዊ ከማድረግ አኳያ ብቻ መሆኑም መታወቅ ይኖርበታል።

ታዲያ ይህን የተቀደሰ ተግባር ለመከወን መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን በጀት መድቦ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ዘርግቷል፤ በመዘርጋትም ላይም ይገኛል። እርግጥ ሁሉም ነገር በአንዴ ሊሟላ አይችል ይሆናል። ይሁንና ምናልባትም ችግሮች ካሉ እንደማንኛውም በማደግ ላይ ያለ ሀገር መንግስትና ህዝብ በጋራ በመሆን ሊፈቷቸው የሚችሉ ይመስለኛል። በዓለም ላይ ያለው የሪሶርስ እጥረት ኢትዮጵያም ይመለከታልና። እናም ሁሉም ነገር የተትረፈረፈና የሞላበት እንዲሁም ልማታዊ ውጥኖች በአንዴ የሚሟላበት ሀገር የሌለ በመሆኑም፤ የሀገራችንም ሁኔታ ከዚሁ አንፃር መታየት አለበት ባይ ነኝ።

በአጠቃላይ በዚህ ፅሑፍ አዘጋጅ እምነት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የሀገራችንን የሰብዓዊ መብት አያያዝ በተመለከተ ያቀረበው ሪፖርት፤ የመረጃ ምንጩ ገለልተኛ ያልሆነና "አንዳንዶች እንደሚገልፁት" በሚሉ አጠራጣሪ ቅፅሎች ጭምር የታመቀ፣ እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዓይነቶችን ፀረ-ኢትዮጵያ ተቋም የፈጠራ ልቦለዶችን በአመዛኙ የተጠቀመ እንዲሁም ያለ ተፈጥሯችን 'እኔን ምሰሉ' የሚሉና ምናልባትም ትክክለኛ ካልሆኑ የሰብዓዊ መረጃ ሰራተኞች የተወሰደ በመሆኑ ሀገራችንን የማይወክል ነው። ከእኛነታችን ጋርም ይህ ነው የሚባል ተዛምዶ የለውም— አይገልፀንም። እናም ሪፖርቱ እውነት ሊሆን የሚችለው በእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችና በመሰሎቻቸው ምናባዊና ልቦለዳዊ ምልከታ ውስጥ ብቻ ነው ማለት ይቻላል።

ለነገሩ የኢትዮ - አሜሪካ ግንኙነት በደርግ ስርዓት ወቅት ከመቋረጡ በስተቀር ረዘም ያሉ ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ባላቸው አሳሳች ተቋማት አማካኝነት

የሚደናቀፍ አይደለም፡፡ እስካሁን ድረስ በጎ ጅምሮችንም ይዞ ዛሬ ላይ የደረሰ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት በፅኑ መሰረት ላይ ተገንብቷል፡፡ ይህ ፅኑ ግንኙነትም የየሀገራቱን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ በፖሊሲና በመርህ የሚመራ እንዲሁም በመከባበርና በጋራ ጥቅም ላይ የተገነባ መሆኑ ይታወቃል፡፡

እርግጥ ዋሽንግተኖች የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ሲመሰርቱም በኢትዮጵያ ላይ ፍላጎታቸውን በኃይል መጫን እንደማይችሉ ተገንዝበው ይመስለኛል፡፡ ለዚህም የራሳቸው ምክንያቶች አሏቸው፡፡ ሀገራችን በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደትና በልማት ላይ ማተኮርዋን ስለሚገነዘቡ፤ በምሥራቅ አፍሪካ ያላትን ጂኦ- ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ስለሚያውቁ ፣ በአካባቢው በሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን እየተጫወተች ያላችውን የላቀ ሚና ስለሚረዱ እንዲሁም በዓለም አቀፍና በአህጉር ደረጃ ያላትን ተቀባይነት ስለሚያጤኑ መሆኑን በምክንያትነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ታዲያ እነዚህ የመንግስታችንና የህዝባችን የማንነት መገለጫዎችና ቁልፍ ተግባራት የአሜሪካ መንግስትም ፍላጎቶች እንደሚሆኑ አልጠራጠርም፤የግንኙነቱ የማዕዘን ድንጋይ እንደሆኑም ጭምር–ማንም የማይነቀንቃቸው።

እነዚህ የግንኙነት መሰረቶች በእኩልነት ላይ በተመረኮዘ ሚዛናዊ ተጠቃሚነት ላይ የሚያጠነጥኑ እንጂ፤ አንዱ “ጌታ” ሌላው ደግሞ ‘ሎሌ’ ሆኖ የሚከናወኑ እንዳይደሉም የአሜሪካ መንግስት እንደሚገነዘበው ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ሀገራችን በአሜሪካ የውስጥ ጉዳይ እጇን ለማስገባት እንደማትፈልግ ሁሉ፤ የዋሽንግተን ሰዎችም ከፖሊሲ አንጻር በውስጥ ጉዳያችን እጃቸውን የሚያስገቡበት ምንም ዓይነት ምክንታዊ አመክንዩ እንደሌላቸው አሳምረው ያውቁታልና፡፡ እናም በመንግስታቸው ስም የሚወጡ ሪፖርቶች (ምናልባትም ሪፖርት የማውጣት ህጋዊ መብት ካላቸው ማለቴ ነው) ትክክለኛነት የሆኑና ከሀገራት ጋር ያላቸውን በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነትን የማያቀረፍዱ እንዲሁም ለአንድ ሀገር ዴሞክራሲያዊ ሂደት እገዛ የሚያደርጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል–በአሉባልታ ላይ የተመሰተ መረጃና ሪፖርት ከአንድ ጊዜ ታይታ ውጪ ለየትኛውም ወገን ምንም ዓይነት ትምህርት ሊሰጥ አይችልምና። አበቃሁ!።